20/10

1692/10


የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
**የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር**
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
**Ministry of Industry**


ቀን 27 የካቲት 2010
Date
ቁጥር 02/1-29/1608
Ref.No

- ለገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
- ለኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን

<u>አዲስ አበባ</u>

**ጉዳዩ:- <u>መመሪያ ስለመላክ፣</u>**

የወጪ ንግድ ቀረጥ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እንዲሁም የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 419/2009 ወጥተው ሥራ ላይ መዋላቸው የሚታወቅ ነው፡፡

ሆኖም አዋጁም ሆነ ደንቡ በኤክስፖርት ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቁ ወይም ጉድለት ኖሮት ከውጭ የተመለሰ ምርት በአገር ውስጥ መሸጥ የሚፈቅድ ቢሆንም ከጠቅላላ የኤክስፖርት ምርት ውስጥ ምን ያህል መሆን እንዳለበት አያመለክቱም፡፡

በመሆኑም ለዚህ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ እና በተለያዩ ምክንያቶች ከውጭ ተመላሽ የተደረገ ምርት በአገር ውስጥ ለመሸጥ የወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2010 7 ገጽ ከዚህ ጋር በማያያዝ መላካችንን እንገልጻለን፡፡

ከሰላምታ ጋር

አህመድ አብተው
ሚኒስትር

<u>እንዲያውቁት፣</u>

ለክቡር ሚኒስትር ዴኤታ/የጨርቃ ጨርቅና ቆዳ ኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ/

<u>ግልባጭ፣</u>

ለጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ ልማት ኢንስቲትዩት
<u>አዲስ አበባ</u>

- ለሴክቶራል ግንኙነትና ማበረታቻ ዳይሬክቶሬት
- ለጨርቃ ጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪ ጥናት ክትትልና ድጋፍ ዳይሬክቶሬት

<u>ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር</u>

# የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ኤክስፖርት ያልተደረገ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ምርት አገር ውስጥ ለመሸጥ ወይም ለማስወገድ የተዘጋጀ የአሠራር መመሪያ

Record & Archive
Ministry of Industry

የካቲት 2010 ዓ.ም

ማውጫ


| አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| 1. መግቢያ | 1 |
| ክፍል አንድ | 3 |
| ጠቅላላ ድንጋጌዎች | 3 |
| 2. አጭር ርዕስ | 3 |
| 3. ትርጓሜ | 3 |
| 4. የተፈጻሚነት ወሰን | 4 |
| ክፍል ሁለት | 4 |
| የመመሪያ አስፈላጊነትና ዓላማዎች | 4 |
| 5. የመመሪያው አስፈላጊነት | 4 |
| 6. የመመሪያው ዓላማ | 4 |
| ክፍል ሦስት | 5 |
| የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ምርት መጠን እና ኤክስፖርት ያልተደረገ ምርት ሽያጭ | 5 |
| 7. የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ምርት መጠን እና ሽያጭ | 5 |
| 8. በተለያዩ ምክንያቶች ኤክስፖርት ያልተደረጉ ምርቶች ሽያጭ አፈጻጸም | 6 |
| ክፍል አራት | 6 |
| የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ምርት የአወጋገድ ስርዓት | 6 |
| ክፍል አምስት | 7 |
| ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች | 7 |
| 9. የሽግግር ሁኔታ | 7 |
| 10. መመሪያውን ስለማሻሻል | 7 |
| 11. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች | 7 |
| 12. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ | 7 |


የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ሪከርድና ማህደር
Ministry of Industry

1. መግቢያ

መንግስት አገራችን ኢትዮጵያን በ2017 መካከለኛ ገቢ ደረጃ ለማድረስ ብሎም ከ40 እስከ 50 ዓመታት ባሉት ጊዜያት ውስጥ ደግሞ በኢንዱስትሪ የዳበረች፣ በኢኮኖሚ የበለጸገችና ለዜጎቿ ከፍተኛ ገቢ የምታስገኝ ደረጃ ላይ ለማድረስ የረጅምና የመካከለኛ ጊዜ ራዕይ ተቀርጸው፣ የተለያዩ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎችም ተነድፈው እና የኢኮኖሚውን ዕድገትና ነባራዊ ሁኔታ መሰረት ያደረጉ እቅዶችና ማስፈጸሚያ መርሃ-ግብሮችም ተዘጋጅተው ተግባራዊ ስደረጉ ቆይተዋል፡፡

አገራችን ባለፉት ዓመታት ያስመዘገበችውን ፈጣን ልማት ዘላቂነት ባለው መልኩ ለማስቀጠል ቀላል ማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ በተለይም ጨርቃጨርቅና አልባሳት ዘርፍ ወሳኝ ሚና መጫወት እንዳለበት በኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጅያችን እና በ2ኛው ዕድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅዳችን ላይ ተመላክቷል፡፡ ተወዳዳሪ የሆኑ እና አቅማቸው የጎለበተ የጨርቃጨርቅና አልባሳት ኢንዱስትሪዎችን ለማፍራት ምቹ የኢንቨስትመንት እና የኦፕሬሽን ሁኔታን በመፍጠር እና የተለያዩ የማበረታቻ ስርዓቶች መዘርጋት እንዳለበት የሌሎች አገራት ተሞክሮዎች ያሳያሉ፡፡

አገራችንም በዘርፉ የተሰማሩ ባለሀብቶችን በወጪ ንግድ እንዲሰማሩ ለማበረታታት የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 እንዲሁም በኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚሰማሩና የተሰማሩ ድርጅቶችን ለመደገፍ የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 417/2009 ወጥተው ተግባራዊ ተደርገዋል፡፡

ይሁን እንጂ በአዋጁ አንቀጽ 23 (3) በምርት ሂደት የጥራት ጉድለት የተገኘባቸው ምርቶች ለውጭ ገበያ መላክ የማይችሉ መሆኑ በኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሲረጋገጥ ተገቢው ቀረጥ ተከፍሎባቸው አገር ውስጥ ሊሸጥ ይችላል በሚል የሚያስቀምጥ ቢሆንም ከጠቅላላው የምርት ትዕዛዝ የምርት ብልሽት መጠን በግልጽ ባለመቀመጡ በአፈጻጸም ሂደት ክፍተት ተስተውሏል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአዋጁ አንቀጽ 25 (2) እና 10 (5) ቀረጥ ያልተከፈለበትን ጥሬ ዕቃ በመጠቀም የተመረተ ምርትን በአገር ውስጥ መሸጥ የሚቻለው የኤክስፖርት ማበረታቻ ስርዓት ተጠቃሚ አምራች ለሚመለከተው የመንግስት መስሪያቤት ቀድሞ ፍቃድ በመጠየቅ ለኤክስፖርት ምርት ጥቅም ላይ ባላዋለው ጥሬ ዕቃ ላይ ሊከፈል የሚገባውን ቀረጥና ታክስ በመክፈል ነው፡፡ በተጨማሪም ወደ ውጭ የተላከ ምርት ወደ ውጭ ከተላከ



Record & Archive
Ministry of Industry

በኃላ ጉድለት ኖሮት ከተመለሰም አሳማኝ ምክንያት በማቅረብ ብቻ እንደሚፈቀድለት የሚገልፅ በመሆኑ አምራቾች በምርት ብልሽት ስም በአገር ውስጥ ገበያ እንዲያዘነብሉ መንገድ የሚከፍት ሆኖ ይታያል፡፡

በሌላ በኩል የኢንዱስትሪ ፓርኮች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 417/2009 አንቀጽ 19 (10 እና 11) ላይ የኢንዱስትሪ ፓርክ ድርጅት የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ወይም ጉድለት ኖሮት ከውጭ ተመላሽ የተደረገ ምርት በጉምሩክ ክልል ውስጥ መሸጥ እንደሚፈቀድለት ቢያስቀምጥም ከጠቅላላ የትዕዛዝ መጠን ውስጥ የብልሽት መጠን ጣሪያ ምን ያክል መሆን እንዳለበት አያመላክትም፡፡

ስለሆነም ይህንን ከላይ የተጠቀሱ ክፍተቶችን ለመሙላት ይቻል ዘንድ በምርት ሂደት የጥራት ጉድለት የሚገኝበት እና የኤክስፖርት ደረጃ ምርት ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች ኤክስፖርት መደረግ ያልቻለ ምርትን በአገር ውስጥ ለመሸጥ እንዲቻል ከጠቅላላ የኤክስፖርት የምርት ትዕዛዝ የጥራት ጉድለት ያለበት ምርት መጠን፣ የሽያጭ ጊዜና ስልት መወሰን በማስፈላጉ ይህ የአሰራር መመሪያ ተዘጋጅቷል፡፡

Ministry of Industry

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

2. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ “የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ እና በተለያዩ ምክንያቶች ከውጭ ተመላሽ የተደረገ ምርት በአገር ውስጥ ለመሸጥ የወጣ የአሠራር መመሪያ ቁጥር 5/2010” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

የቃሉ ትርጉም ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

3.1 **“አዋጅ”** ማለት የወጪ ንግድ ማበረታቻ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 768/2004 ነው፡፡

3.2 **“ደንብ”** ማለት ስለኢንዱስትሪ ፓርኮች የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 417/2009 ነው፡፡

3.3 **“ሚኒስትር ወይም ሚኒስቴር”** ማለት እንደአስፈላጊነቱ የኢንዱስትሪ ሚኒስትር ወይም የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው፡፡

3.4 **“ባለስልጣን”** ማለት የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ነው፡፡

3.5 **“የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ምርት”** ማለት ላኪ ወይም አምራች ድርጅት ገዢው በሰጠው የምርት ጥራት ደረጃና መስፈርት መሠረት ሳያመርት ቀርቶ በገዢው የጥራት ተቆጣጣሪ ባለሙያ ከደረጃ በታች የተባለ ምርት ነው፡፡

3.6 **“ከውጭ ተመላሽ የተደረገ ምርት”** ማለት ኤክስፖርተር ወይም ላኪ ድርጅት ገዢው ባሰቀመጠው የማቅረቢያ ጊዜ ያልቀረበ ወይንም ገዢው ጋር ከደረሰ በኋላ ጉድለት መኖሩ ተረጋግጦ ተመላሽ የተደረገ ምርት ነው፡፡

3.7 **“የጉምሩክ ክልል”** ማለት የኢትዮጵያ የግዛት ክልል ነው፡፡

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
ሪከርድ ማህደር
Record & Archive

4. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ የወጭ ንግድ ማበራታቻዎችን የሚጠቀም እና ምርቱን ሙሉ በሙሉ ወደ ውጭ አገር ለመላክ ከመንግስት ጋር ስምምነት የፈፀመ በኢንዱስትሪ ፓርክ እና ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ የሚገኝ የጨርቃጨርቅና አልባሳት አምራቾች ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## ክፍል ሁለት
## የመመሪያ አስፈላጊነትና ዓላማዎች

5. የመመሪያው አስፈላጊነት

5.1 በምርት ሂደት የተበላሹና ለውጭ ገበያ መላክ የማይችሉ እንዲሁም ወደ ውጭ ተልከው የተመለሱ ወይም የኤክስፖርት ደረጃ ኖሯቸው ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች ኤክስፖርት መደረግ ያልቻሉ ምርቶች ለአገር ውስጥ ገበያ ማቅረብ የሚያስችል ወጥ የሆነ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

5.2 በምርት ሂደት ሊኖር የሚችለውን አገራዊ አማካይ የብልሽት ወይም የጉድለት መጠን በማስቀመጥ ሙሉ በሙሉ ምርቱን ወደ ውጭ ለመላክ የተስማማ አምራች በምርት ጥራት ጉድለት ወይም ትዕዛዝ መሰረዝ ምክንያት ወደ አገር ውስጥ ገበያ ላይ እንዳያተኮር የክትትልና ቁጥጥር ስርዓት ማበጀት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ፣

6. የመመሪያው ዓላማ

ይህ መመሪያ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡፡

6.1 የወጪ ንግድ የቀረጥ ማበረታቻ ስርዓት በአግባቡ ተግባር ላይ ስለመዋላቸውና የሚጠበቀውን የውጭ ምንዛሬ ግኝት ዕድገት እና ሌሎች ውጤቶች ማስገኘታቸውን መከታተልና ማረጋገጥ፣

6.2 አምራቾች የጥራት ጉድለት ያለበት እና የኤክስፖርት ደረጃ ሆኖ በተለያዩ ምክንያቶች ኤክስፖርት ለማድረግ ያልተቻለ ምርት ለአገር ውስጥ ገበያ ለመሸጥ የሚያቀርቡት ጥያቄ ወጥነት ባለው መልኩ ምላሽ መስጠት፣

6.3 ሙሉ በሙሉ ምርቱን ወደ ውጪ አገር ለመላክ ስምምነት ያላቸው አምራቾች ወደ አገር ውስጥ ገበያ እንዳያዘነብሉ የአሰራር ስርዓት መዘርጋት፣

## ክፍል ሦስት

### 7. የጥራት ጉድለት ያለበት ምርት መጠን እና የኤክስፖርት ደረጃ ኖሮት በተለያዩ ምክንያቶች ኤክስፖርት ለማድረግ ያልተቻለ ምርት ሽያጭ

#### 7.1 በጥራት ጉድለት የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ምርት መጠን እና ሽያጭ

7.1.1 የምርት ብልሽት መጠን ከጠቅላላ ትዕዛዝ እንደ አገራት የዕድገት ደረጃ፣ የሚጠቀሙት የቴክኖሎጂ፣ ምርቱን የሚያመርተው ባለሙያ የክህሎትና ዕውቀት ደረጃ፣ የሚጠቀሙት ግብዓት የጥራት ሁኔታ፣ የሚከተሉት የአመራረት ሂደት ወይም ስርዓት እና ሌሎች ጉዳዩች ላይ የሚመሠረት ይሆናል፡፡

7.1.2 ከሌሎች አገራት ጋር የሚሰሩት ገገርዎች ተቀባይነት ያለው የብልሽት መጠን እንደ ምርቶቹ ዓይነትና ባህርይ ወይም ውስብስብነት የሚለያይ ሲሆን የአገራችን ነባራዊ ሁኔታ በማገናዘብ የአገራችን የአልባሳት ተቀባይነት ያለው የብልሽት መጠን ከጠቅላላው የኤክስፖርት ትዕዛዝ እስከ 5% ድረስ ብቻ ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

7.1.3 በምርቱ የተለየ ባህርይ ምክንያት ከ5% በላይ ብልሽት ወይም ጉድለት መጠን መጨመር ቢያስገድድ ሚኒስቴሩ ጉዳዩን በተለያየ መንገድ መርምሮ በልዩ ሁኔታ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡

7.1.4 ምርቱ የኤክስፖርት ደረጃ ያሟላ ስለመሆኑ በአምራቹ ወይም ገገርው ከሚሰጠው ማረጋገጫ በተጨማሪ ሚኒስቴሩ አጠቃላይ የምርት ጥራት ፍተሻ ወይም ኢንስፔክሽን ማድረግ ይችላል፡፡

7.1.5 በኢንስፔክሽን ወቅት በገገርዎች በቋሚነት የተወገደ (permanently rejected) ምርት በምርቱ የውስጠኛ ክፍል ምልክት (Stamp with “Rejected for Buyer X”) ተደርጎባቸው ለብቻ መቀመጥ አለባቸው፡፡

7.1.6 አለም አቀፍ ገገርዎች የብራንዳቸውን ስም (Brand Image) ለመጠበቅ ሲሉ በተለያዩ ምክንያቶች የተወገዱ ምርቶች ለተጠቃሚ እንዲሸጡ የማይፈቅዱ በመሆኑ ከገገርዎቹ ፍቃድ በማግኘት ወይም የብራንድ ምልክት (Brand Label) በማንሳት አምራቾች በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ (በታህሳስ ወር እና ሚያዚያ ወር የመጨረሻ ሁለት ሳምንታት) እንዲሸጡ ይፈቀድላቸዋል፡፡

...y of Industry

7.1.7 አምራቾች የኤክስፖርት ደረጃ የማያሟሉ ምርቶችን በማንኛውም ጊዜ በዓይነት ወይም ስታይል፣መጠንና በገርዎች አደራጅተው መያዝና በሚኒስቴሩ መረጃውን በሚጠየቁበት ወቅት ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

7.2 የኤክስፖርት ደረጃ ቢኖራቸውም በተለያዩ ምክንያቶች ኤክስፖርት መደረግ ያልቻሉ ምርቶች ሽያጭ አፈጻጸም

7.2.1 አምራቾች ምርቱ ወደ ውጭ ከተላከ በኋላ ጉድለት ኖሮት የተመለሰ ወይም በተለያዩ ምክንያቶች ገዥያቸው እንደማይቀበል የገለፀላቸው ስለመሆኑ የተሟላ መረጃ ማቀረቡ ሲረጋገጥ እና ምርቱን ኤክስፖርት ማድረግ ካልተቻለ በአገር ውስጥ ገበያ መሸጥ ሊፈቀድ ይቻላል፡፡

7.2.2 ከኤክስፖርት ተመላሽ ምርቶች የኤክስፖርት ደረጃ ከማያሟሉ ጋር ሳይቀላቀሉ ለብቻቸው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

7.2.3 ተመላሽ ምርቶች ስለመመለሳቸው በቂ ማስረጃ ቀርቦ ከታመነበት ብቻ በዓመት ሁለት ጊዜ (ታህሳስ ወር እና ሚያዚያ ወር የመጨረሻ ሁለት ሳምንታት) ሽያጭ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

ክፍል አራት

8. የኤክስፖርት ደረጃ ያልጠበቀ ምርት የአወጋገድ ስርዓት

8.1 የምርት ብልሽት ስለመኖሩ ወይም ከውጭ ተመላሽ ስለመደረጉ በሚኒስቴሩ ተረጋግጦ ለሽያጭ ሲፈቀድ፡፡

8.2 የሽያጭ ቦታ በኢንዱስትሪ ፓርክ ውስጥ ለሚገኙ አምራቾች በኢንዱስትሪ ፓርኩ ውስጥ በተዘጋጀ ልዩ ቦታ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ከሁለት ሳምንት ለማይበልጥ ተከታታይ ቀናት አስፈላጊውን ቀረጥና ታክስ ለባለሥልጣኑ በመክፈል ሊሸጠው ይችላል፡፡

8.3 ሙሉ በሙሉ ምርቱን ወደ ውጪ እንዲልክ የሚጠበቅበት ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጪ የሚገኙ አምራች በፋብሪካው ቅጥር ግቢ ውስጥ ወይም በአካባቢው በሚዘጋጅ ልዩ ቦታ በዓመት ሁለት ጊዜ ብቻ ከሁለት ሳምንት ለማይበልጥ ተከታታይ ቀናት አስፈላጊውን ቀረጥና ታክስ ለባለሥልጣኑ በመክፈል መሸጥ ይችላል፡፡



Ministry of Industry

8.4 አምራቹ በፍላጎቱ ምርቱን አገሪቱ ውስጥ በሕግ አግባብ ለተቋቋመ የበጎ አድራጎት ድርጅት በስጦታ እንዲያበረክት የሚበረታታ ከመሆኑም በላይ ይህን ሲያደርግ በስራ ላይ ባለው የጉምሩክ አዋጅ መሠረት በምርቶቹ ላይ መክፈል ከሚጠበቅበት ቀረጥና ታክስ ነፃ ይሆናል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 9. የሽግግር ሁኔታ

ይህ መመሪያ ከመዘጋጀቱ በፊት በኢንዱስሪ ፓርኮች ውስጥ እያመረቱ ያሉ እና ከኢንዱስትሪ ፓርኮች ውጪ ሙሉ በሙሉ ምርታቸውን ኤክስፖርት ለሚያደርጉ ፋብሪካዎች እስካሁን በተለያዩ ምክንያት የተጠራቀሙ የጥራት ጉድለት ያለባቸው እና ከኤክስፖርት ተመላሽ የሆኑ ምርቶችን ለሚኒስቴሩ እንዲያሳውቁ ተደረጎ በሚወሰን የጊዜ ማዕቀፍ ውስጥ አስፈላጊውን ቅድመ ሁኔታ በማሟላት በልዩ ሁኔታ እንዲሸጡ ይፈቀድላቸዋል።

### 10. መመሪያውን ስለማሻሻል

ይህ መመሪያ በኢንዱስትሪ ሚኒቴር የበላይ አመራር እንደ ሁኔታው እየታየ በየጊዜው ሊሻሻል ይችላል።

### 11. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው መመሪያዎች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዩች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

### 12. መመሪያው የሚጸናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ ከየካቲት 30 ቀን 2010 ዓ ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር